

## ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን

- ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ ለሰው ሁሉ ቸር ነበር፤ ሰዎችንም ሁሉ ይወድ ነበር። አንዳንድ ሰዎች ግን ይህ የጌታ ፍቅርና ርህራሄ ያልተገባቸው ነበሩ። እነዚህ ሰዎች ያስፈልጋቸው የነበረው የእርሱ ቁጣ ወይንም ተግሳፁ ነበር። ኃይማኖተኞች ይመስላሉ። ነገር ግን ፍቅር የሌላቸውና ለሌሎች ፍፁም ርህራሄ ያልነበራቸው ናቸው።

- ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ፈሪሳውያን ተብለው የሚጠሩትን የአይሁድ የኃይማኖት መሪዎች እጅግ ነቀፋቸው። ፈሪሳውያን ከሚያገኙት ገቢ አስራት (አንድ አስረኛ) ለማውጣት ጥንቁቆች ነበሩ። ሆኖም አብዛኛውን ጊዜ አስራት ሲያወጡም ሆነ ለእግዚአብሔር ሌላ አይነት ስጦታ ሲሰጡ ሰዎች እንዲያዩአቸውና እንዲያደንቋቸው ስለሚሹ የሰዎችን አትኩሮት ይጋብዛሉ። የሙሴን ሕግ በመጠበቃቸው ከመጠን በላይ ይመካሉ። ሆኖም ለሌሎች ምንም ግድ የላቸውም።

- ኢየሱስ እነኝህን ሰዎች በሚገባ ካማረና ከተቀባ መቃብር ጋር ያመሳስላቸዋል። መቃብር ምንም ያህል ውብ ቢሆን በውስጡ የሚገኘው የሞተ ሰው አፅም ብቻ ነው። ፈሪሳውያንም የእግዚአብሔር ነቢያት የሚያመጡት መልእክት ለእነርሱ ካልጣማቸው ነቢያቱን ከመግደል ወደኋላ የማይመለሱ ሰዎች ነበሩ። መጥምቁ ዮሐንስ ኃጢአታቸውን እንዲናዘዙና እንዲጠመቁ ሲሰብካቸው ሊሰሙት ፈቃደኞች አልነበሩም።

- ልክ እንደፈሪሳውያን የኢየሱስ ክርስቶስ ቁጣ የተገባቸው ሌሎች የኃይማኖት መሪዎች ደግሞ ፀሐፊዎች ተብለው የሚታወቁት ናቸው። ፀሐፊዎች የሙሴን ሕግ በእጃቸው ይገለብጡ ነበር። የሙሴን ሕግ ለሕዝቡ

በሚገባቸው ቋንቋ እየተረጎሙ ያስተምሩ ስለነበርም በጣም ተፈላጊዎች ነበሩ። በጣም ተፈላጊዎች ነን ብለው ስለሚያስቡም ዋጋው እጅግ ውድ የሆነ ዘርፈ ረጅም ቀሚስ ይለብሱ ነበር። በምኩራቦችም ሆነ በሌሎች እግዚአብሔር በሚመለከባቸው ስፍራዎች የክብር ቦታ መርጠው መቀመጥ ልማዳቸው ነበር። ተራው ሕዝብም 'ረቢ' ወይንም መምህር ብሎ እንዲጠራቸው አጥብቀው ይሹ ነበር። ተራው ሕዝብም ፈሪሳውያንን እንደ እውነተኛ ኃይማኖተኛ ይቆጥራቸው ነበር።

- በመሠረቱ ፈሪሳዊ መሆን በራሱ መጥፎ ነገር አይደለም። ጥሩ ነገር ነበር። ኢየሱስ የተፀየፈው በብዙዎቹ ፈሪሳውያን ውስጥ የነበረውን ግብዝነት ነው። እውነትን ይሰብካሉ፤ እውነተኛው ሕይወታቸው የሚያሳየው ግን የእግዚአብሔርን ሕግ የሚታዘዙ መምሰላቸው ነው። እውነቱ ግን ሌሎችን ማክበርም ሆነ ለሌሎች ማሰብ የሚባል ነገር በእነርሱ ዘንድ የሚታወቅ ነገር አለመሆኑ ነው። እንዲህ አይነት ሰዎችን 'ግብዞች' ብለን እንጠራቸዋለን።

- ሰዱቃውያን የሚባሉት ደግሞ ባለጠጋ የሆኑ አይሁዳውያን የኃይማኖት መሪዎች ነበሩ። ሰዱቃውያን ከሞት በኋላ ትንሳኤ የለም፤ መላእክትም የሉም የሚል እምነት ነበራቸው።

- የአይሁድ ሸንጎ 71 አባላት ሲኖሩት ሁሉም ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ነበሩ። ሆኖም አንድ ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባናል። ይኸውም በዚያን ዘመን የነበሩ ሁሉም የኃይማኖት መሪዎች ኩሩዎቸና አስመሳዮች ናቸው ብለን እንዳናስብ ነው። ምናልባትም ሶስቱን ዝነኞችና መልካም ፈሪሳውያን ሳታውቋቸው አትቀሩም። እነርሱም ሐዋርያው ጳውሎስ፣ ኒቆዲሞስና የአይሁድ ሸንጎ አባል የሆነውና አስተዋዩ ገማልኤል ናቸው።

*ይህ የፈሪሳውያንና የሰዱቃውያን ታሪክ የሚገኘው በማቴዎስ 23፡ 1 – 36 ውስጥ ነው።*

http://gardenofpraise.com